# ሙግት

አቶ መንግሥቱ ለማ

አያ ነጭ አምላኩ ፈጣሪው ፈረንጅ
ታሪክ ይሆንና ታዛቢ ፈራጅ
የወንዝህ ልጅ ሆኖ ያገርህ ጠበቃ
ተጠየቅ ይልህል አታውቅ እንደሆነ፤
ያሬድ “ ዋይ ዜማ ” ሲል ዘመረ? ዘፈነ?
ጾመ ድጓ ማነው?
ድጓዣ ማነው?
አባትዮው ማነው፥ ማነው ልጅዮው?
ኃይለኛው ታላቁ ራስ ወልደ ገብርዔል
ትክክል ፈራጅ ዳኛ ነው ሲባል
አንድ ልጁን ለምን ሰደደው ገደል?
“ እረኝነት ይሻል ከመሆን ካህን”
ብሎ የተቀኘው ማነው፤ መች፤ለምን?

ሠረገላ ብርሀን የሚባል ሰው ነበር
የጎጃም ምድር ጉድ የሐበሻ ታምር
አያ ነጭ አምላኩ አልሰማህም እንዴ
ያገርህ አርበኛ ዘምቶ ከውጋዴ
ሲወቃው መሞቱን ታንኩን በጎራዴ?

እሰጥ! ይህ አይደለም “ አለመሰልጠን”
ወይ “ በድንቁርና ሕይወት ማባከን”
እንደመሰከረ ያ ቴዎድሮስ
ሽጉጡን አጉርሶ ሽጉጡን ሲጎርስ.....

አያ ነጭ አምላኩ ተረተሃል እንጃ
የጣልከው የተውከው ሆኗል መቶ ታምሳ ::
አንጃ የጣልከውን ያገርህን ዜማ
የሕዝብህን ቋንቋ የዘርህን ግርማ
ያገርህን ጨዋታ ጭፈራ ዘፈን
ካገርህም ልማድ መልካም መልካሙን::

አያ ነጭ አምላኩ ምለህ ተፈጠም
አይለምደኝም  ብለህ ማጋበስ መልቀም
ፈረንጅ የጣለውን ያልጣለውንም
የፈረንጅ የሆነ ቅዱስ ነው ማለት
ይውረድ እንደወጣ ከራስህ ውርደት!
ሰውነትህን አትካድ፤ ሕዝብህን አትክዳ
አንት ለዘሩ ባዳ ለሐገሩ ዕንግዳ።

( “ የፖለቲካ እስረኛ የነበሩ ግጥሞች” ከተባለው ሰብስብ የተወሰደ )